አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like The River

# የተከበሩ የአዋሽ ባንክ ባለአክሲዮን

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ታህሳስ 23 ቀን 2017 ዓ.ም በቁጥር ኢካገባ/608/17 በፃፈው ደብዳቤ በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 መሰረት የሰነድ ሙዓለ ንዋይ (አክሲዮን) ባለቤትነት መዝገቦች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስር በተቋቋመ ማዕከላዊ የሰነድ መዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በተዘጋጀ ኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሂሳብ መዝገብ ስርዓት መተካት ያለበት በመሆኑ፣ ይህን ለመፈፀም እንዲቻል የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶችን (የባለ እክሲዮኖችን) መረጃ እስከ ጥር 22 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ዝግጁ እንድናደርግ አሳውቆናል።

በመሆኑም የፋይዳ ካርድ ቁጥርዎን (FAN)፣ የአድራሻ ለውጥ አድርገው ከሆነ አዲሱን እድራሻ፣ ኢ.ሜል፣ ስልክ ቁጥር፣ የቤት ቁጥር፤ ሀገር፣ ክልል፣ ከተማ፣ ክ/ከተማ፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ ባለአክሲዮኑ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነ የታክስ መለያ ቁጥር (TIN) እና የድርጅቱ ወኪል ሙሉ መረጃ አዋሽ ባንክ ዋና መ/ቤት አጠገብ በሚገኘው ኢያሜክስ ህንፃ ምድር ላይ በባንኩ ባለአክሲዮኖች አካውንትስ ዋና ክፍል ወይም አቅራቢያችሁ በሚገኛ የአዋሽ ባንክ ቅርንጫፎች በአካል በመቅረብ እንዲያሳውቁ በአክብሮት እንጠይቃለን።

**አዋሽ ባንክ**